የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ-ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

12th Year No. 41
ADDIS ABABA - 5th May, 2006


## ማውጫ


"የወጪ ንግድ ሽልማት አሰጣጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፳፮/፲፱፻፺፰"
........................................................ ገጽ ፫ሺ፬፻፸፯


## CONTENTS


"Export Prize Awards Council of Ministers Regulations No. 126/2006".
........................................................ Page 3477


### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፳፮/፲፱፻፺፰
### የወጪ ንግድ ሽልማት አሰጣጥን ለመወሰን የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፱ አንቀጽ ፵፯ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የወጪ ንግድ ሽልማት አሰጣጥ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፳፮/፲፱፻፺፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ ፤

፩. "የወጪ ንግድ ቀን" ማለት በወጪ ንግድ አፈጻጸም የተሻለ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ሰዎች ሽልማት እንዲሰጥበት በየዓመቱ በሚኒስቴሩ የሚወሰን ቀን ነው ፤

፪. "ላኪ" ማለት የኢትዮጵያ የወጪ ምርቶችን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው ፤

፫. "ዓለም አቀፍ ስታንዳርድ" ማለት በዓለም አቀፍ ገበያ የሚፈለጉ የወጪ ምርቶች ማሟላት ያለባቸው የጥራትና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ስታንዳርድ ነው ፤

፬. "የወጪ ምርት ግብዓት" ማለት ልዩ ትኩረት ለተሰጣቸው የወጪ ምርቶች በግብዓትነት የሚያገለግልና በሀገር ውስጥ የሚመረት ምርት፣ ማሸጊያ ፣ ኬሚካል ወይም አክሴሰሪ ነው ፤

### *Council of Ministers Regulations No. 126/2006*
### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS ON EXPORT PRIZE AWARDS*

These regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47 of the Commercial Registration and Licensing Proclamation No. 67/1997.

1. *Short Title*

These Regulations may be cited as the "Export Prize Awards Council of Ministers Regulations No. 126/2006".

2. *Defintions*

In these regulations unless the context requires otherwise:

1) "Export day" means a day to be designated every year by the Ministry for awarding export prizes to best performing persons engaged in the export sector;
2) "Exporter" means a person that supply Ethiopian export products to overseas markets;
3) "International standards" means quality and related standards that need to be fulfilled by export products demanded in the global market;
4) "Export product input" means any product, packaging material, chemical or accessory produced locally and used as an input for priority export products;


ያንዱ ዋጋ 2·30
Unite Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Ngarit Gazeta P.O.box 80001

፭. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ፤

፮. "ሚኒስቴር" ማለት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው ።

፫. <u>የወጪ ንግድ ሽልማት የመስጠት ዓላማ</u>

የወጪ ንግድ ሽልማት የመስጠት ዓላማ በወጪ ንግዱ ዘርፍ የተሰማሩ ሰዎች ለሚደርጉት ጥረትና ለሚያስመዘግቡት ውጤት ዕውቅና በመስጠት ለማበረታታትና በውጤት ላይ ያተኮረ የውድድር መንፈስ በመፍጠር የወጪ ንግዱን እንቅስቃሴ ቀጣይነት ይበልጥ ማጠናከር ይሆናል ።

፬. <u>የወጪ ንግድ ሽልማት መቋቋም</u>

፩. የሚከተሉት የወጪ ንግድ ሽለማቶች በዚህ ደንብ ተቋቁመዋል ፤

ሀ) የላቀ የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሽልማት ፤

ለ) አዲስ የወጭ ምርት ሽልማት ፤

ሐ) የወጪ ምርት ገዢ ሽልማት ፤

መ) የወጪ ምርት ግብዓት አቅራቢ ሽልማት ፤

ሠ) የወጪ ንግድ ድጋፍ ሰጪ ሽልማት።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ሽልማቶች ዓይነትና ይዘት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ።

፭. <u>ለወጪ ንግድ ሽልማት ብቁ ስለመሆን</u>

፩. የላቀ የወጪ ንግድ አፈጻጸም ሽልማት በማንኛውም የወጪ ንግድ ዘርፍ የተሻለ የውጪ ምንዛሪ ገቢ ለሚያስመዘግቡ ላኪዎች ይሰጣል ።

፪. አዲስ የወጪ ምርት ሽልማት የኤክስፖርት ስብጥርን ከማስፋት አኳያ ቀድሞ ውጪ ገበያ ያልገቡ ምርቶችን ለውጪ ገበያ በማቅረብ የተሻለ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ ላኪዎች ይሰጣል ።

፫. የወጪ ምርት ገዢ ሽልማት ኢትዮጵያ ወደ ውጪ የምትልካቸውን ምርቶች በመግዛት የተሻለ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ ገዢዎች ወይም ለወኪሎቻቸው ይሰጣል።

፬. የወጪ ምርት ግብዓት አቅራቢ ሽልማት የተሻለ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ የወጪ ምርት ግብዓት አቅራቢዎች ይሰጣል ።

፭. የወጪ ንግድ ድጋፍ ሰጪ ሽልማት በወጪ ንግዱ ዘርፍ ለተሰማራው የንግዱ ኅብረተሰብ ድጋፍ በመስጠት የተሻለ አፈጻጸም ለሚያስመዘግቡ የመንግሥትና የግል ተቋማት ይሰጣል ።

፮. በዚህ አንቀጽ መሠረት ሽልማት የሚገባቸውን ተወዳዳሪዎች ለመምረጥ የሚያስችሉ ዝርዝር መስፈርቶች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ ።

፮. <u>መራጭ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>

የወጪ ንግድ ሽልማት ተወዳዳሪዎችን የሚመርጥ ኮሚቴ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት አግባብነት ካላቸው የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አካላት ተውጣጥተው የሚሰየሙ አባላት የሚገኙበት ኮሚቴ ይቋቋማል ።

፯. <u>የወጪ ንግድ ሽልማት ስለመስጠት</u>

የወጪ ንግድ ሽልማት የወጪ ንግድ ቀን በየዓመቱ በሚከበርበት ጊዜ ይሰጣል ።

5) ''Person'' means a natural or juridical person;

6) ''Ministry'' means the Ministry of trade and Industry.

3. *Objective of Awarding Export Prizes*

The objective of awarding export prizes shall Be to acknowledge the efforts and achievements scored by persons involved in the export sector and thereby create result oriented competitive environment to ensure further improvements in the export sector performance.

4. *Establishment of Export Prizes*

1) The following export prizes are hereby instituted:
   (a) Excellent Export Performance Prize;
   (b) New Export Products Prize;
   (c) Export Product Buyers Prize ;
   (d) Export Product Input Suppliers Prize; and
   (e) Export Support Prize.

2) The types and substances of the prizes referred to in sub-article (1) of this Article shall be specified by directives to be issued by the Ministry.

5. *Eligibility for Export Prize Awards*

1) Excellent Export Performance Prizes shall be awarded to best performing exporters in any export sector.

2) New Export Product Prizes shall be awarded to best performing exporters exporting new export products.

3) Export Product Buyers Prizes shall be awarded to best performing Ethiopian export product buyers or their agents.

4) Export Product Input Suppliers Prizes shall be awarded to best performing input suppliers.

5) Export Support Prizes shall be awarded to best performing governmental and private organizations in providing support to the business community engaged in the export sector.

6) The specific selection criteria for export prize award winners pursuant to the provisions of this Article shall be prescribed by directives to be issued by the Ministry.

6) *Selection Committee*

A committee, composed of representatives of relevant governmental and private sector organizations, shall be established in accordance with directives of the Ministry to select export prize award winners.

7) *Awarding Export Prizes*

Export prizes shall be awarded during annual celebrations of export days .

፰. <u>የወጪ ንግድ ሽልማት ተሸላሚዎች ጥቅሞች</u>

የወጪ ንግድ ሽልማት ተሸላሚዎች ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት የሚከተሉት ጥቅሞች ይጠበቁላቸዋል ::

፩. በመሳሪያ ኪራይ ወይም በፋናንስ ኪራይ ሥርዓት የቅድሚያ ተጠቃሚ የመሆን ፤

፪. የዓለም አቀፍ ስታንዳርዶችን ለማሟላትና ማረጋገጫ ለማግኘት በሚደረጉ ጥረቶች በወጪ መጋራት ስርዓት ድጋፍ የማግኘት ፤

፫. በወጪ ንግድ ብድር ዋስትና ሥርዓት ለማይሸፈኑ የግብርና ምርቶችም በሥርዓቱ ተጠቃሚ የመሆን፤

፬. በውጭ ሀገር በሚዘጋጁ የንግድ ኤግዚቢሽኖች ለመካፈል በወጪ መጋራት ሥርዓት ድጋፍ የማግኘት ፤

፭. በሀገር ውስጥ በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች ምርቶችን ለማቅረብ የቦታ ኪራይ ክፍያ ድጋፍ የማግኘት ፤

፮. በሚኒስቴሩ በሚታተሙ መጽሔቶች ፣ ብሮሸሮች፣ ኒውስሌተሮችና ዌብሳይት ድርጅቶቻቸውንና ምርቶቻቸውን የማስተዋወቅ ፤

፯. በመንግሥታዊ ተቋማት በሚሰጡ ሥልጠናዎች ቅድሚያ የማግኘት ፤

፰. በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት በሚቋቋም የክብር መዝገብ የመመዝገብ፤

፱. ያገኟቸው ሽልማቶች በመገናኛ ብዙሀን እንዲገለጹላቸው የማድረግ ፤

፲. ወደ ሀገር ውስጥና ወደ ውጭ ሀገር በሚደረጉ የንግድ ተልዕኮዎች ተሳትፎ ቅድሚያ የማግኘት፤

፲፩. የሕዝብ በዓላት አከባበር ሥርዓቶችና በመንግሥት የሚደረጉ ግብዣዎች በሚካሄዱባቸው ሥፍራዎች ልዩ ክብር ለሚሰጣቸው እንግዶች በሚዘጋጀው ቦታ የመቀመጥ ፤

፲፪. ወደ ውጭ ሀገር ሲጓዙና ሲመለሱ ልዩ ክብር በሚሰጣቸው እንግዶች ደረጃ የመስተናገድ ::

፱. <u>የወጪ ንግድ ሽልማት ማስፈጸሚ በጀት</u>

የወጪ ንግድ ሽልማት ማስፈጸሚያ ወጭ ከመንግሥት በሚመደብ በጀትና ከስፖንሰርሽፕ በሚገኝ የፋይናንስ ምንጭ የሚሸፈን ይሆናል ::

፲. <u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል::

፲፩. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፪ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

8) Privileges due to Awardees of exports Prizes

Awardees of export prizes shall, as determined by directives of the Ministry, be entitled to:

1) preference to get service under equipment lease or financial lease schemes;
2) cost sharing support in efforts to meet international standards and thereby get accreditations;
3) access to Exporters Credit Guarantee Scheme for agricultural products not already included in the scheme ;
4) cost sharing support to participate at international exhibitions;
5) financial support to cover space rentals to participate at national exhibitions;
6) Promote their organizations and products through the magazines, brochures, newsletters and website of the Ministry;
7) Preference to participate in trainings offered by public institutions;
8) be registered in the honorary register kept by the Prime Minister's Office;
9) publicity of their prize awards through the media;
10) preference to participate in inward and outward trade missions;
11) seats reserved for guests with VIP status at places where public ceremonies and government receptions are held;
12) VIP status while travel departures from and arrivals to Ethiopia .

9. *Budget for Export Prize Awards*

The financial costs of awarding export prizes shall be covered by government budgetary appropriations and sponsorship funds.

10. *Power to Issue Directives*

The Ministry may issue directives necessary for the proper implementation of these Regulations.

11. *Effective Date*

These Regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta .

Done at Addis Ababa this 18 th day of August , 2006

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE